የተፃፈ ቀደር ይቀየራል እንዴ

" እንዴ እንዴ የተፃፈ ቀደር ይቀየራል እንዴ?" አላቸው ደረሳው ለሸይኹ::

" እንዴ ዱዓ ቀደርን ዘወትር እንደሚታገለው ኢታውቅምን?!" አሉት ሸኾቹ::

"ቀደር" ማለት በኛ ጉዳይ አላህ ቀድሞ የወሰነው ጉዳይ ነው:: አም አንዳንድ በተከታተይትና ሳይታከቱ፣ ሳይሠለቹ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ የሚደረግ ዱዓ ከጥንካሬው የተነሳ ቀደርን ሊጥለው ሁሉ ይታረባል:: በዚህ ላይ ደግሞ ደጋግ የአላህ መላእክት ጭምር ያግዙታል:: "አላህ ሆይ የዚህን ባርያህን ዱዓ ስማ!" እያሉ አላህን ይለምኑለታል:: ወዳጄ ሆይ! ዱዓ የአላህ መሻት ነው:: ለዱዓ የሚያነሳሳም አላህ ነው:: አስታውሰህና ጊዜ ወስደህ እጅህን ከፍ አንድታደርግ ያደረገህ አሱ ነው:: አንዳንድ ሰው ቀደሩን ያውቅ ይመስል ዱዓ ኢድርጌ ቀደሬን ላልለዉጥ ነገር ምን አስለፋኝ ይላል:: ሰበብ ፈጥሮ ከዱዓ ይሳነፋል:: አላህን ከመለመን ይዘናጋል::

ወዳጄዋ! ቀደርህን ሳታውቅ ቢቃ ቀደሬ ነው አይቀየርም ብለህ ቁጭ ባልከበት አትሙት:: ይገርማል!! ሰው ሳይሞት እንዴት እጅ ይሠጣል!:: ሞኝ አትሁን ነገሮችን አላህ ነው የሻብኝ ብለህ አሥራቸው ቁጭ ብለህ አትደብደብ:: ሳትታሰር ታስሬያለሁ ብለህ ላለመንቀሳቀስ ምክንያት አትፍጠር:: በል አሁኑኑ ተነስ:: ከዚያ ካልወደድከው፣ ካደከመህና ካደቀቀህ ቀደር ወደዚያ ወደተሻለዉና ወደምትመኘው ቀደር ለመሸሽ ታገል:: ሰው ከማይሻለው ነገር ወደሚሻለው፣ ከከረምት ጨለማ ወደ ብራው ፀደይ፣ ከሐዘን እንጉርጉሮ ወደ ብሩህ ደስታ ለመሸሽ መሞከሩ አላህ የሻለትን ነገር አለመውድ ነው ማለት አይደለም:: ከመጥፎ ቀደርም ወደተሻለ ቀደር እንሸሻለን:: ከጥበትም ወደ ሰፋት፣ ከችግርም ወደ ድሎት እናማትራለን:: ቢድህነት ሙቱ ያለን የለም:: በበሽታ ማቅቁ ፈውስ አትፈልጉ አይባልም:: አላህ በሽታንም መድሃኒትንም ፈጠረ:: ሀብትንም ድህነትንም አሰገኘ:: መልካም ፀጋ ለመልካም ሙአሚን የተገባ ነው:: ፕንዙብ ቢያገኝ ይመፀዉታል:: ጤና ቢኖረው ደግ ይሠራበታል::

ወዳጆቼ! ሁሌም የተሻለዉን ነገር ተመኙ:: ታዲያ ይህ ሁሉ ሊሳካ የሚችለው በተለይ በሌሊት ሰዓታት በሚደረጉ ዱዓኦች፣ ሶላዋትና ኢስቲግፋር በማብዛት፣ ሱጁድ በማርዘምና አዝካሮች ላይ በማዘውተር ነው::

አላህ ሆይ! ያለንበትን ሁኔታ ወደተሻለ ሁኔታ ለውጥልን::

አያረፍን ...

ዱንያ ላይ ስትኖር በቻልከው መጠን ሁሉ ለፈጣሪህ አደር። የአላህን ትዕዛዝ ለመተግበር ደፋ ቆና በል። አሱ ባዘዘህ ቦታ ላይ የቻልከውን ያህል ተግኝ። ሰገደ ሲልህ ስገድ፣ ስጥ ሲልህ ስጥ፣ እድርግ ሲልህ አድርግ፣ ተው ሲልህ ተው፣ ሁም ሲለህ ውም። ከግዴታም አልፈህ ሱንናን ለመተግበር ተጭጨርጨር። ወደሱ በሚያቀርብህ ነገር ሁሉ ወደርሱ ለመቅረብ ታገል። ታገል መሜዋ። በርታ ወንድሜዋ።

****

እኛ የእደምና ሐዋ ልጆች የተሠራነው ከሥጋ፣ አጥንትና ደም ነው። ግና ከብረት እንደተሠራ ሰው መኖር በሚያስፈልግበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ወጣያለ፣ ብርቱና ጠንካራ መሆን ይኖርብናል።

ወዳጆቹ ... ዱንያ በብዙ መልኩ ተለዉጣለች፣ ፊተናዋ በዝቷል፣ ኑሮዋም በጣም ከብዷል። አንዳንዴማ ምድር ላይ ይሆን ያህል ዘመን ታግሰንና ታግለን በሕይወት መቆየታችን በራሱ ትልቅ ሰነሔት ነው ያስብላል።

ወዳጆቼ! ሶላት እና አስተግፋር ለብዙ ችግሮቻችን አሁንም ሁነኛ መፍትሄዎቻችን ናቸው። በየሱጫችን መሃል እናስታውሳቸው።

የፍትህ አንገብጋቢነት

• ነቢያችን ሶ.ዐ.ወ. ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱት በካፊሮች መካከል መኖርን ጠልተው አይደለም፤ ግፍና በደል ስለበዛባቸው እንጂ።

• ሶሐቦቻቸው ወደ ሐበሻ እንዲሰደዱ ያዘዙትም የያኔ ንጉሷ ሙስሊም ስለሆነ አይደለም ፍትሃዊ ስለሆነ እንጂ።

• ከዲን ይልቅ ወገን ቢቀርብ ኖሮ ነቢዩ ከመካ ሸሽተው ወደ መዲና ባልተጠጉ ነበር። ግና ገዳዩ የሀቂዳና የፍትህ ገዳይ ነው። መምረጥ ግድ በሆነብን ሰዓት ላይ በወገን ከሚመስለን ይልቅ በዲን የሚመስለንን መምረጥ እንዳለብን ማሳያ ነው።

• ፍትህ የንግሥና መሠረት ነው። ፍትህ ያለበት ሁሉ አገራችን ነው።

እኛንም ዱንያ ትዞረናለች እኮ ..

አንዳንድ ሚስኪን ወዳጆቻችን ምድር ላይ ያለን አይመስላቸዉም እኮ። ሰው መሆናችንን ግዑምር ይረሳሉ። መላኢካ እንመስላቸዋለን። የሰው ባህሪ እንዳለን እያስታዉሱም። በሰው ላይ የሚደርስ ችግር በኛ ላይ የሚደርስ አይመስላቸዉም። ስንመክር፣ ስናስታዉስ፣ አብሽሩ አይዟችሁ በርቱ ስንል፣ ከነርሱ የምንበልጥ እንመስላቸዋለን። ሰዎችን ስናገናና፣ እንዲሰሩና ፈጣሚ እንዲሉ ምክንያት ለመሆን ስንጥር ስለሚያዩን እኛን ችግር የሚያገኘን አይመስላቸዉም። ጠንካሮች እና ፍዉም አድርገው ይስሉናል። ዱንያ የምትሞያየርብን፣ ቀናትም ፊት እንደሚነሱን፣ ሁኔታዎች እንደሚለዋወጡብን ... ለነርሱ ሞን ባስታወሰልን!!። እንዳንዶች ... በነርሱ ቤት ያለ ችግር እኛም ቤት አንዳለ፣ እነርሱን ያገኘ ሀመም ለኛም እንዳልተመለሰ እንዲያዉቁ እንፈልጋለን። ሕይወት ዙጉበድጓ እንደምታሠራን ንገሯቸው፣ መከራ እንደሚፈራረቅብንም አሰረዷቸው።

ወዳጆቼ ... ሞጥ ያልን ብርቱዎች እና ጥዑሞች አድርጋችሁ አታስቡን። እንደከሞለን፣ እናዝናለን፣ ዐባያችን ይለዋወጣል፣ እንኮሚኮሚለን፣ እንቆጣለን፣ ከሰው እንጣላለን። ሆድ ይብሰናል፣ ዘግተን እናለቅሳለን፣ ብቻችንን ሆነን እንተከዛለን። ሳቃችን ይደበገዛል፣ ዉስጣችን ይታመማል፣ ልቦናችን ይታወክል፣ ሰላማችን ይናጋል። ዱንያ ሰው ልጅ ላይ የምታደርሰዉን ነገር ሁሉ በኛም ላይ ታደርሰናለች። እንታመማለን እንሸራለን፣ እንወድቃለን እንነሳለን፣ እናዝናለን እንደሠታለን።

መካሪዎች፣ ኡስታዞች፣ ዑለሞች፣ መምህራን፣ ዐለፊዎች ሰው ናቸው። ዱንያ ላይ ሰዉን የሚያገኘው ፊተና ሁሉ ያገኛቸዋል። በሚወዱት ሰው ሞት ይፈተናሉ፣ በልጅ መጥመም ይፈተናሉ፣ በትዳር መናጋት ይፈተናሉ፣ በቀልብ ድርሎት ይፈተናሉ። ግና የሚለያቸው መታገላቸዉና መታገሳቸው ሊሆን ይችላል።

ወዳጄ! እሱ ጠንካራ ነው፣ ጎበዝ ነው፣ አይሸነፍም .. የምንለው ሰው በርግጥ እየተቃጠለ እየበራ ቢሆንስ ማን ያውቃል። እየሳቀ እያለቀሰ ቢሆንስ። ከራሱ ችግር ይልቅ የሰው ችግር በልጦበት ቢሆንስ ማን አየ። ጭሱ አይታይም እንጂ በያንዳንዱ ሰው ቤት ዉስጥ እሳት አለ። ዱንያ በሰው ላይ የምታደርገዉን ሁሉ በመካሪዎችና አስታዋሾች ላይም ታደርጋለች። እነርሱ ለሷ ቀይ መስመር አይደሉምና።

መለያየት ክፉ ...

እትዘን ወዳጄዋ፡፡ ዱንያ ሕያውትም ሞትም ናት፡፡ ሕያውት መገናኘትም መለያየትም ናት፡፡ ዱንያ ላይ በሕያውት እጋጣሚ ያገኘነው፣ የተዋወቅነው እና አብረን የኖርነው ከሙተዋወቅም አልፈን የወደድነው ሰው ሁሉ አስከዘላለሙ አብሮን ይኖራል ማለት እይታሰብም፡፡ ከዱንያ ቁናት በአንዱ ቀን ወይ እንለየዋለን ወይ ይለየናል፡፡ በሞት ይሁን በሕያውት እንለያያለን፡፡ እስከመጨረሻው አንለያይም ብለን ከሰነበተ ተለያለናል መለላችሁ፣ አንረሳዉም ብለን ስንቱን ከነመፈጠሩ ፈጅምር ረስተናል፡፡

መገናኘት ድንቱ ነው፤ መተዋወቅ አጋጣሚ ነው፤ መላመድ ዕጣፈንታ ነው፡፡ በዚህ መሃል ደግሞ በቅርብ ይሁን በሩቅ ጊዜ ዉስጥ መለያየት የሚባል ነገር አለ፡፡ አሱ መኖሩን እንዳንረሳ፡፡ መለያየት መኖሩን አለመርሳት ድንጉት ከፃፍነወደው እና ከተላመድነው ሰው በተለያየን ጊዜ ሊኖር የሚችለውን ሐዘንና ትካዜ ያቃልልናል፡፡

መተዋወቅ የአላህ መሻት ነው፡፡ መለያየት ዉስጥም የርሱ ፈቃድ አለበት፡፡ ሰንሊያያ አያንዳንዱ ሰው የራሱ አሻራ ጥሎብን ይሄዳል፡፡ አንዳንዱ ስሜቱ የማይጠፋ ደስታ አልብሶን ይሄዳል፡፡ ሊላው የተወጋ ልብ ትቶልን ይሄዳል፤ ከፊሉ የማይለቅ ትዝታ ጥሎብን ይጠፋል፡፡

የሰው ልጅ ላይለያይ አልተፈጠረም፡፡ አንደም ሕይወት ወይም ሞት የተባለው ከሰተት ይለያዮዋል፡፡ ሁሉም ከሰተቶች ግን አስተምረዉን ያልፋሉ፡፡

ሰው መገናኘቱ መልካም ነው፡፡ ጥሩ ከሆነ ጥሩ ወዳጅ ይሆናል፤ ያስተምራል፤ ያጠነክራል፤ ያበረታል፤ የሕይወት ልምድ ይሠጣል፤ መልካምነቱ ወደኛ ተጋብቶ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም ተጠቃሚ ያደርገናል፡፡ መጥፎ ከሆነም መሄዱ ማለፊያ ነው፡፡ ለበለጠ ጥፋት እንዳንጋለጥ ያተርፈናል፡፡ ከአኺራችን መበላሸት ይታደገናል፡፡ ከከፋቱም እናርፋለን፤ ከማስቸገሩ እንድናለን፡፡

አንዳንድ ሰው መለያየትን ሲያስብ መተዋወቅን ይፈራል፡፡ ግና መለያየት ከሕይወት መገለጫዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዱንያ ባህሪ ነው፡፡ ባህሪዋ እንደሆነ ካወቃችሁ መለያየትን አትፍሩ፡፡ መተዋወቅንም አትፍሩ፡፡ የዱንያ የተለያዩ ባህሪዎች ማወቅ፤ ሞት መኖሩን፤ መለያየት አንዳለ ማስታወስ በዚህች ዓለም ላይ ተረጋግተን እንድንኖር ያግዘናል፡፡ ነገሮችን ስታውቁ አትፈሩም፤ አትደነግጡም፡፡ ሶባሐል ኸይር!

ለምችን ከኃጢኣት እንዳይወጡ ማገት...

የሰው ልጅ ሁሌም በአንድ ሀሳብ ላይ ሊይኖርም መቸስ። ብዙ ነገሮች ሀሳቡን ያስለዉጠኑታል። ዕውነት ዋናው ነው። የሆነ ጊዜ ላይ መልካም መስሎት የጀመረው ነገር የሆነ ጊዜ ላይ ሲደርስ መጥፎ እንደሆነ ይገለጥሊታል። የሆነ ጊዜ ትክክል መስሎት የጀመረዉ ነገር ቆይቶ ደግሞ ስህተት እንደሆነ ይገባዋል።

አንዳንድ ጊዜ አንድም ባለማወቅ ሁለትም በመዘናጋት ከሆነ ሰው ጋር የኃጢኣት ሸሪካ ልትሆን ትችላለህ። የሆነ ጊዜ ላይ ደግሞ ስህተት መሆኑን አውቀህ፣ ወንጀል እንደሆነ ተረድተህ፣ አላህ አየተቆጣብህ መሆኑን ተገንዝበህ ከዚህ አስፀያፊ ድርጊት ለመውጣት ታስባለህ። ቢቃ ይህን ነገር አላህ ሊይወደዉም ስትለው ሸሪካህ ግን ሀሳብህን ላይደግፍህ፣ ዉሳኔህንም ላይቀበል ይችላል። ከዚህም አልፎ ጭራሽ ሊውቅስህና ጥፋተኛ ሊያደርግህ ሁሉ ይሞክራል። የሚያኮርፍና የሚጣላም ብዙ ነው። የከረምክበትን የኃጢኣት ፋይል መገ ሚስጠርህንም ሊያወጣ የሚያስፈራራህም ይኖራል። መጀመርያ ለምን ጀመርከ አሁን ለምን ማቆም ፈለግክ ብሎ በሱ ላይ የሠራኸው ሸፍጥ አስመስሎ ሁሉ ሊያቀርብ ይችላል።

ያንተ ኃጢኣትን ለማቆም የመወሰን አርምጃህ ለአንዳንዱ ፈጽሞ ሊይዋጥለትም። ፈዝም መስሎ የሚታየው አለ። ጉዳዩ ሁሌም አብረን አንዳከር ነው። አብረን አንደጀመርን አብረን አንጥፋ ዓይነት ይመስላል። የሚገርመው የዚህ ዓይነቱ ሰው ይህን መጥፎ ወንጀል ወደ ቆንጆ ሐሳል አንቀይረው ብትለው አንኳን የማይቀበል መሆኑ ነው። ወስጡ አውነታዉን ቢያውቅም አንዲሁ አንደተጀጀለና አንዳጃጀለ መቆየት ይፈልጋል። ሐራም ላይ ይበረታል፤ ሐላል ላይ ሲደርስ ያንገራግራል። የዚህ ዓይነቱ ሰው ዓላማው ሁሉ አንተንም ሆነ ራሱን በኃጢኣት ዉስጥ ማገት ነው። በጭቃ ዉስጥ ማቆየት ነው። በአሾህ ዉስጥ ማኖር ነው።

በርግጥኝነት የምነግርህ ነገር ብኖር በይሉኝታም ሆነ በሌላ ምክንያት አብረኸው በቆየህ ቁጥር ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ሕይወትህ ምንም ጠብ የሚልልህ ነገር አይኖርም። ዛሬ ነገ ይሻሻላል ይለወጣል ብለህ ዕድል ብትሠጠው ብትጠብቀው ብትጠብቀው ... ፈጽሞ አይሻሻልም አይለወጥም። ምክንያት አየፈጠረ ያግትሃል፣ አያስመሰለ ያቆይሃል፣ አሁን አሁን አያለ ያዳክምሃል፣ በመጨረሻም ለዉርደት ይዳርግሃል። አብረህ በምትቆይባቸው ጊዜያት ሁሉ የህሊና ሰላም አይኖርህም፣ ዉስጥህ ከመናጋት አይወጣም።

ስለዚህ ጋጢአትን ለሙተው የማንንም ምክር አትጠብቅ፤ ከማንም ጋር አትመካከር። ጨከነው፣ ወሰነጪና ቆርጠው ካልተጪት በስተቀር እሱ ፈጽሞ የማያተው ደሮ መሆኑን እንድታውቅ ይሁን። ከጋጢአት ጋር ረጅም ጉዞ መጓዝ ከአገር እንደመወጣት ነው። በሄድክ ቁጥር መመለሻው ከባድ ነው የሚሆነው።

ለዚህ ዓይነቱ ሰው _ በፊት ለምን ጀመርከ! አሁን ለምን መተው አሰብከ ለሚለህ ብልጣብልጥ ምን ትለዋለህ መሰለህ። መስሎኝ ጀመርኩ አልመሰል ሲለኝ መተው አሰብኩ በለው። ላላውቅ ጀመርኩ ዕውቀት ሲደርሰኝ መተው ፊለግኩ በለው። ቢያምን ባያምን፤ ቢቀበል ባይቀበል የራሱ ጉዳይ ነው። ሀሊናህ ካረፈና አላህ ከተቀበለህ በቂ ነው። አላህ ደግሞ ለሱ ብለህ የተውከዉን መጥፎ ነገር በጥሩ ሊተካልህ ቃል ገብቷል።

ወዳጆቹ! ከናንተ ጋር የጀመረዉን ጋጠአት መተው ለፊለገ ሰው እንዴ! ለምን! ብላችሁ አትገረመበት። ይሁን እንጂ አይሆንም አትበሉት። ጋጠአት ተሰየን ብላችሁ አታልቅሱ። ሰው ለመልካም ነገር ቀረብኝ ብሎ ያለቅሳል፤ አናንተ ጋጠአት ሄደብኝ ብላችሁ እንዴት ታለቅሳላችሁ! ይህ አሳፋሪ ነው። ባይሆን እዚህ ላይ አናቁም ያለን ሰው መርሐባ በሉት። ወንጀል ይቅርብን ያለን ሰው አድንቁት እንጂ አትውቀሱት። ሀሳቡንም በመልካም እነጂ በመጣፎ አትጠርጥሩ። የጀመረው ሆነበሎ አናንተ ሊጎዳ እንደሆነም አታስቡ። ካቻላችሁ አብራችሁ ተዉ፤ ወደ አላህ ቶብቱ። ካልቻላችሁ ጥሩ መስነሃል፣ መንገዱን ጨርቅ ያድርግለህ፣ መልካመን ሁሉ ይወፍቅህ በሉት። ለራሣችሁም የአላህን ተውፊቅ ለምኑ።

ወደ መልካም አገር ለመሄድ ያሰበን ሰው እንቅፉት አትሁኑበት። ወደ አላህ ልሂድ ያለን ሰው ማገት ከአገታዎች ሁሉ የከፋው ነው። ባለቤቱም በሁለት ወንጀል ይጠየቃል። አንድም ራሱ በሚሠራው ወንጀል፤ ሁለትም ሌላዉን ወንጀል ዉስጥ ለማስቀረት በመታገል ወንጀል።

ወንጀል ልተው ያለ ሰው ሊበረታታ እንጂ ሊነቀፍ አይገባም። ለኛም ጥሩ አስተማሪ አና የህሊና ደወል ሊሆነን ይገባል። እንደዉም " እኛስ ወደ አላህ ለመመለስ ምን አገደን !" ብለን ራሣችንን መጠየቅ አለብን። "አስጀምሮ መንገድ ላይ ተወኝ" የሚለው ለቅሶ ለጋጢአት ሲሆን አይሠራም። ማፈግፈግ ለአላህ ሲሆን አልል ያለ ድል ነው አትጠራጠሩ ወዳጆቹ። መመለስ ወደ አላህ ሲሆን ከፍታ ነው። መሸነፍ ፈጠረን አምላክ ሲሆን ማሸነፍ ነው። ጌታዬ ሆይ ሲትራህን።

አያረፍን_

- የሚመከርህ ሰው የራሱ ቁሰል ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም።
- የሚረዳህም ሰው ካንተ በላይ ኖሮት ላይሆን ይችላል።
- የሚጨነቅልህም ቢሆን እሱ ራሱ ከሀሳብ ማዕበል ነፃ ሆኖ አይደለም።

ለሰው ማሰብና መጨነት ከራስ ይልቅ ለላን ማሰበለጥ (ኢሣር) ዉጤት ነው። የሚወዱትን ወንድም እህት በሚወዱት ነገር ላይ ማስቀደም የደጋግ አበው መንገድ ነው። ታድያ ይህ አሳቢ በገንዘብ ብቻ አይደለም የሚከናወነው። በቃልም በተግባርም ይገለፃል።

****

ወዳጄዋ ... ዛሬ ላይ የተዉን ሰዎች ሁሉ ትናንት ረጅም ጉዞ አብረዉን እንደሚጓዙ፣ ፈጽሞ እንደማይተዉንም በተደጋጋሚ ቃል ሲገቡልን የነበሩ ናቸው። የሚገርመው ደጋግመዉና አጥብቀው ቃል የሚገቡልን፤ ቀድመው የሚሄዱት እነርሱ መሆናቸው ነው። በዚህች አጭር ጊዜ ዉስጥ በሕይወታችን ዉስጥ ስንት ሰው መጣ ስንትስ ሄደ!። በነሻጣ ቃል አትግባ፣ ከገባህ ቃልህን ለመጠበቅ ታገል።

ሶባሐል ኸይር!

- አምሸቶ ነግቶም ጭንቅላቱ እንደከበደው የሚነሳ ሰው ብዙ ነው፤
- ተኝቶ ተነስቶም የትናንት ሀሳቡ ያልለቀቀው ፍጡር በርካታ ነው ፣
- ቀን ቀንን ቢተካም ችግሩ፣ ሰጉቱ፣ መከራው፣ ሀመሙ ... የስንገር ታከል ፈቀቅ የማይልለት ሞልቷል፣
- በየማለዳው ‘ያው ነው የኛ ነገር፤ ምን አዲስ ነገር አለ ብለህ እያለ የሚያጉረመርም እህህ እያለ የሚኖር ብዙ ነው፤
- ዱንያ ቀኝም ሆነ ግራ ሆና ልታነጋ ትችላለች፣
- ግና አላህ ዘንድ ተወዳጁ ትንፋሽ ተፋሉል ነው። ማመስገንና መልካም ነገርን ተስፋ ማድረግ ነው።
- ስለ ሁሉም ነገር ሹክር ይገባህ የስትንፋሴ ጌታ፣ የሩሌ ባለቤት በሉ።

  ባነጋችሁ ቁጥር “አስበሐና ወአስበሐልሙልከ ሊላህ። ወልሐምዱ ሊላህ።” ማለትን አዘውትሩ።